የሰ/መ/ቁ. 71316

ግንቦት 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገፈ ፈጅ ዮሴፍ ቀውዬ

ተጠሪ፡- ለገሠ ጌታሁን ጠበቃ አቶ ለገሠ ማሞ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በንብረት ላይ የሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 እንደተደነገገው መልሶ ለማስነሳት የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በከሣሽ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በተከሣሽ አቶ ኃይሉ ሃብቴ መካከል በነበረው የብድር ገንዘብ ክርክር ከሣሽ ለፍርድ አፈፃፀም ዋስትናው ይሆነው ዘንድ በተከሣሽ እና በባለቤቱ ስም ተመዝግቦ በሚገኘው ት/ቤት ላይ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት አማካኝነት ታግዶ እንዲቆይ የሚያስችል ትዕዛዝ ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡

የአሁን ተጠሪ በበኩል ህዳር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ይህ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረት ከተከሣሽ እና ከባለቤቱ ጋር በተደረገ የሽያጭ ስምምነት በግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 80,000.00 ገዝቻለሁ፡፡ ይህንንም የሽያጭ ውል ያደረግነው በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ነው፡፡ እንደውሉ ሻጭ ሊፈጽሙ ስላልቻሉ ለሸቢዳኖ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤ ስመ-ሀብትነቱን ወደ ስሜ ለማዞር ስሞክር መታገዱን ተረድቻለሁ፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በህግ አግባብ በገዛሁት ቤት ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካችም የዕግድ ትዕዛዙን የማይነሳበትን ምክንያት በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በቀድሚያ የተመለከተው የሲዳማ ዞን ከፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ለማንሳት የሚያበቃ ክርክርና ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የዕግዱ ትዕዛዝ አይነሣም የሚል ዳኝነት ሲሰጥ፤ ይግባኝ ሰሚው የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ የሽያጩ ተግባር የተፈፀመው የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለሆነ የሽያጭ ውሉም በሚመለከተው አካል በመመዝገቡና በህግ የሚጠየቀውም መስፈርት ውሉ በመዝገብ መፃፍን እንጂ የስመ ሃብትነት ዝውውር በግልጽ

በሕግ እንደ ማሚያ ስላልተመለከተ ቀደም ሲል የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣ ይገባል በማለት ሽሮታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የተለየ ዳኝነት ጉድለት የለበትም በማለት የአሁን ተጠሪን ሳይጠራ አመልካችን በማሰናበቱ ይህ የሰበር ክርክር ሊቅርብ ችሏል፡፡

በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በይዘቱ ከዚህ በፊት ካቀረቡት የተለየ አይደለም፡፡ የተለየው ነጥብ ቢኖር ቀደም ሲል በሻጭ ላይ ባቀረቡኩት ክስ መሠረት አስወስኜ የፍርድ ባለመብት መሆኔም ይታወቅልኝ የሚለው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአሁን ተጠሪ በፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣልኝ ይገባል ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሣ ይገባል ለሚለው ዳኝነቱ መሠረት ሆኖ የተያዘው የአሁን ተጠሪ የት/ቤቱን የሽያጭ ውል በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤቱ አድርጓል፤ አስመዝግቧል የሚለውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ፊት ውል የማድረግ ተግባር አስፈላጊነቱ ከውል አመሠራረት ጋር የተያያዘ፤ ውሉ ተደርጓል፣ አልተደረገም? የሚለውንና በውሉ ስለተካተቱት ዝርዝር ጉዳዮች (As to any terms of the contract) ወደ ፊት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ክርክር እንዳይፈጠርና እንዳይነሣ ለማድረግ ሲባል የውል አደራረግን ሂደት የማረጋገጥ (authentication) መሆኑንና ውጤቱም በተዋዋይ ወገኖች መካከል ለሚነሳ ክርክር እልባት በመስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

አንድን ንብረት በሽያጭ ውል ገዝቻለሁ፤ ስለሆነም በዚህ ንብረት ላይ ያለ እኔ ሌላ ሶስተኛ ወገን መብት የለውም በማለት ማናቸውንም ሶስተኛ ወገን ለመመለስ ግን ት/ቤቱ በሚገኝበት ሥፍራ በሚገኘው ንብረትን መዝግቦ ለመያዝ ስልጣን በተሰጠው ማዘጋጃ ቤት የምዝገባ ሥርዓቱ ሊከናወን እንደሚገባ በንብረት ህጉ እና በውል ህጉ ከተመለከቱት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር በእነዚህ በውል አደራረግ ሥርዓት ማሚያነት በቀረበው ውልን የማረጋገጥ ተግባር እና ሶስተኛ ወገንን ለመጠበቅም ሆነ ለመመለስ እንዲያስችል የተቀመጠውን የምዝገባ ሥርዓት (registration) ምንነትና ተግባር በውል ካለማጤን በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት የተሰጠበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ አስወሰኜ በፍርድ ባለመብትነት ደረጃ ላይ እገኛለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር እንደ አግባብነቱ ይኸው ንብረት ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል ለማድረግ በተከበረ ጊዜ የቀደምትነትን መብት ለማስረዳት የሚያግዘው ካልሆነ በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 የተሰጠን የእግድ ትእዛዝ ለማስነሣት የሚያስችል አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የዕግድ ትእዛዙ ሊነሳ ይገባል በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 67656 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 51779 መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. በአንፃሩ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19703 ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የህግ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ